# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 301 የካቲት 7 2006 ገጽ 1


ወያኔና ሎሌዎቹ ህዝብን የሚያታልሉበት ካርድ ከእንግዲህ አልቋል። አዋርደውናል፣ ገድለውናል፣ አስረውናል፣ አስርበውናል፣ ለስደት ዳርገዉናል፣ አለያይተውናል። ከዚህ በላይ ምን ሊያደርጉን ይችላሉ? ስለዚህ ቀኑ መሽቶባቸዋል እና በፍጥነት ሊወገዱ ይገባል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የፍትህን በር እየዘጉ ስለፍትህ ማዉራት አይቻልም በማለት ህዝብ ኃ/ማሪያም ደሳለኝን አወገዘ

የሕወሃት ፍጹም አገልጋይና ጉዳይ ፈጻሚ ሀይለማሪያም ደሳለኝ ሰሞኑን ባሰማው ንግግር የተበሳጩ ታዛቢዎች ፍትህን ገድሎ ከቀበረው በኋላ ስለፍትህ ማውራት ሹፈት ነው። በተለይ ወያኔ ሕወሃት በዚህ መልኩ ለማውራት የሞራል ብቃት የለውም በማለት ጥያቄ ማንሳታቸው ታውቋል።

እየተደረገ ያለውንና የምናየውን እንዘግባለን ያሉ ጋዜተኞች፤ ሕዝባችን ዴሞክራሲያዊ መብቱ ይጠበቅ፣ የመናገር፣ የመጻፍ፣ የመሰብሰብና በሰላማዊ መንገድ ሰልፍ የመውጣት መብቱ የከበርለት ያሉ የነጻነት ታጋዮች፤ እንዲሁም እምነታችን በሚፈቅደው መንገድ እናምልክ፣ ወያኔ በሃይማኖታችን ጣልቃ አይግባብን ብለው ተደብቀው ሳይሆን ፊት ለፊት የጠየቁ አማኞች በአሸባሪነት በሚከሰሱባት ሀገርና ለዚህም የፍትህ ስርአቱ ለአገዛዙ ፍጹማዊ የሆነ አድሎ በተሞላበት መንገድ በሚያገለግልበት በዚህ ሰአት ሃይለማሪያም ደሳለኝ ስለፍትህ መናገሩ ፍጹም አሳፋሪና አበሳጭ ነው የሚሉ ጥቂቶች አይደሉም።

የሳምንቱን የእረፍት ቀናት ቅዳሜና እሁድን ሳይቀር በወያኔ ጉልበተኛ ቅልብ ወታደሮች ተደብድበው የዛሉና በዚህ ወይም በዚያ አካባቢ የሽብር ስራ እንሰራ ነበር እንዲሉ የተገደዱ ንጹሃን ኢትዮጵያዊያንን በፖሊስ ጽ/ቤትና በተለያዩ የወያኔ ቢሮዎች ጭምር እየዞሩ በማስማልና ቃል በመቀበል የሚያገለግሉት ይወያኔ የፍትህ ስርአት ተብየ ተቀጣሪዎች ሞልተው በተረፉባት ኢትዮጵያ የፍትህ ስርአቱ የሁሉም የበላይ፣ ሁሉንም በአማካይ የሚያገለግና ግልጽነት የተሞላበት መሆን አለበት እያሉ ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## አዲስ አበባና የክልል ከተማዎች ኑና እንታገል በሚሉ በራሪ ወረቀቶች መሸፈናቸዉ ተሰማ

በሀገሪቱ ሰሜን፣ ደቡብና ደቡብ ምስራቅ ባንደንድ አካባቢዎች ተኩስ የቀላቀሉ አንዳንድ ሕዝባዊ እንቢተኝነቶችን ማስቆም ተስኖት ጭንቅ ውስጥ ያለው ህወሃት፤ ሰሞኑን ደግሞ አዲስ አበባን ጨምሮ በሌሎችም አካባቢዎች የተነሱ እንታገል መንፈስ ያላቸው በራሪ ወረቀቶች መበተናቸውና በየግድግዳውም ላይ አንዳንድ መፈክሮች ተጽፈው መገኘታቸው ሳያንስ ለጉዳዩ የሚጠየቅ ግለሰብ ወይም ቡድን ለጊዜው አለመኖሩ ፋሽስት ወያኔን ጭንቅ ውስጥ እንደከተተው ታውቋል።

ባሁኑ ሰአት በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል አስተማማኝ ሰላም አለ ለማለት አይቻልም የሚሉት ውስጥ አዋቂ ምንጮቻችን ፣ በሁሉም አካባቢዎች ህወሃት ሕዝባዊ ፖሊስ የሚለው ነገር ግን ካቅሙ በላይ የታጠቀ ጦር፣ ህዝባችንን እንዳይወጣና እንዳይገባ በማድረጉ ሂደት ከፍተኛውን ድርሻ የሚወስደው ፌደራል የሚባለው የወያኔ አጋዚ ጦር እንዲሁም አንዳንዴ መደበኛው የወያኔ ጦር ሳይቀር የሚታዩበት አጋጣሚ ጥቂት አይደለም በማለት በአጽንኦት ይገልጻሉ።

ምናልባትም ከችግሩ ጋር በተያያዘ በግምት አፍሶ ማሰር ሊኖር እንደሚችል የጠቆሙት ምንጮቻችን እንዲህ አይነቱ የግምት እስር በተገቢው መንገድ ድርጅታችሁን አላገለገላችሁም ብሎ የጠረጠራቸውን የራሱን የህወሃትን አባላትንና ደጋፊዎችንም ሊጨምር እንደሚችል አልሸሸጉም።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ህወሃት ደንበራችንን አሳልፎ በመስጠቱ፣ የዜጎቻችንን ክብር ለማስጠበቅ ባለመቻሉ፣ በሀገራች በተንሰራፋው ዓይን ያወጣ አድሎና በመሳሰሉት የተዛቡ አሰራሮቹ ቅር የተሰኙ የወያኔ አባላትና ደጋፊዎች ይህን ጎጠኛ ድርጅት እየጣሉ በመኮብለላቸው ወያኔ ከላይ እስከ ታች ለተደጋጋሚ ግምገማ መዳረጉ አይዘነጋም።

## ወያኔ ለራሱ ለሚገነባዉ የባቡር መስመር በኢትዮጵያ ህዝብ ስም በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ መበደሩ ተሰማ

መቀሌን ከጂቡቲ ጋር ለማገናኘት ይገነባል የተባለው የባቡር መስመር፡ የወልድያና የሰመራ ከተሞችን እንደሚያቋርጥ የተነገረ ሲሆን መዳረሻው ፖርት ታጁራ ጂቡቲ ሲሆን፡ 675 Km ርዝመትም ይኖረዋል ተብሏል። ይህ የባቡር መስመር ከጎረቤት ሃገሮች ጋር የሚኖረው የንግድ ትስስርን ያጠናክራል ተብሎ የተገመተ ሲሆን፡ በተለይ ከደቡብ ሱዳን ጋር የሚኖረው ትስስር ተጠቃሽ ነውም ተብሏል። ስምምነቱ ከሁለት ሳምንት በፊት የተፈረመው ይህ የባቡር መስመር ዝርጋታ በስራው የቱርክ፡ የቻይናና ሌሎችም ተቋራጮች እንደሚሳተፉበት ለማወቅ ተችሏል።

ጉዳዩ በርካታ ቁጣን የተላበሱ አስተያየቶችን እያስተናገደ እንደሆነ የተነገረለት ይህ የባቡር መስመር ዝርጋታ አጠቃላይ ወጭው 1.7 USD ሊሆን እንደሚችል የተገመተ ሲሆን ጉጅሌው ወያኔ ቀሪውን 300 ሚ. ዶላሩን እንደሚሸፍን ታውቋል።

ጉጅሌው ወያኔ ለወደፊት አላማው የትግራይ ሪፖብሊክን ለመመስረት የቅድመ ዝግጅት አንዱ ማሳያ ነው የሚሉ በርካታ ወገኖች፡ የንግድ መዳረሻ ከሆነችው የሃገሪቱ ዋና ከተማ ማለትም ከአዲስ አበባ ለምን እንዳይነሳ ተፈለገ ሲሉ እየሞገቱ ሲሆን፡ በሌላ ወገን እንደተለመደው ትውልድን በዕዳ ዘፍቆ ለማለፍ እንጂ ይህ የስራ ማስኬጃ ገንዘብ በቱባ የጉጅሌው ሙሰኞች ተመዝብሮ ለመጭው ትውልድ የዕዳ ሸክም ሆኖ ያልፋል ሲሉ አስተያየታቸውን የሚሰጡም በረካቶች መሆናቸውን ዘጋቢያችን ከተለያዩ የሶሻል ሚዲያዎች ላይ የቃረመውን አስተያየት በማጠናከር አድርሶናል። ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## የህወሃት ታጋዮች አርስ በርሳቸዉ እየተሿከቱ የሀገሪቱን ሀብትና ንብረት እየዘረፉ ከአገር በመጥፋት ላይ ናቸዉ

የፋሽስቱ ወያኔ ታጋዮች መጠነ ሰፊ ሃብት በዝርፊያ በማካበት በሃገሪቱ ተወዳዳሪ የሌላቸው ባለሃብቶች መሆናቸው ይታወቃል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በሙስኞቹ ታጋዩች መሃከል እየተነሱ ያሉ የርስ በርስ አለመግባባቶች ወደ ክስ ማምራታቸውን ተከትሎ ሚሊየነር ታጋዬች ይፋ እየወጡና ለዕስር እየተዳረጉ መሆናቸውና፡ ራሳቸውን ደብቀው ያሉ በርካታ በሙስናው የተጨማለቁ ታጋዩች ከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ መሆናቸውን ምንጮቻችን ዘግበዋል።

ከሰሞኑ በሙስና የተከሰሱት ወልደስላሴ ጋር በግብረ አበርነት የተከሰሱት የህወሃት ታጋዩ የወልደስላሴ ወንድም ታጋዩ ዘርአይ ወልደስላሴ ላይ ጸረ-ሙስና ኮሚሽን ባደረገው ማጣራት ግለሰቡ በተለያዩ ባንኮች በስሙ 5 ሚሊዮን ብር ማስቀመጡን፣ አዲስ አበባ ቤቴል ሆስፒታል አካባቢ በ74 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ግንባታ እያካሄደ መሆኑን ፣ በአፋር ክልል ደግሞ ከ1 ሚሊዮን 400 መቶ ሽ ብር በላይ በሆነ ወጪ የእርሻ ኢንቨስትምንት እያከናወነ መሆኑን የተጋለጠ ሲሆን በተጨማሪም በስሙ 2 ሚሊዮን 700 ሺ ብር ግምት ያላቸው 2 ሎደር መኪኖች መገኘታቸውን አጋልጧል። ይህ ግለሰብ የመከላከያ ሚኒስቴር የነበረ ሲሆን ተቋሙን ሲሰናበት በመጨረሻ ይከፈለው የነበረው ወርሃዊ ደሞዝ 532 ብር ብቻ እንደነበርም ተመልክቷል።

( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ወያኔ አዲስ አበባና አማራ ክልል ዉስጥ ወጣቶችን እያፈሰ በማሰር ላይ መሆኑ ተነገረ

ጭንቀት ውስጥ የገባው ፋሽስቱ ወያኔ በርካታ የአማራ ክልል እና አዲሳባ ወጣቶችን በግንቦት ሰባትና ሌሎች ፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት አላቸው በሚል መሰረተ ቢስ ክስ ወደ ወህኒ እያጌዘ መሆኑ ተነግሯል። ዘጋቢዎቻችን እንዳደረሱን፡ በአካቢዎች የስልክና ኢንተርኔት አገልግሎት ተቋርጧል በርካታ ቅጥረኛ የፌደራስ ፖሊሶች ተበትነው ወጣቱን እያፈሱ መሆኑ ታውቋል። በተያያዘ ዜና በአዲሳባ በለሊት የሚፃፉና የሚለጠፉ የተቃውሞ ጽሁፎች ተበራክተዋል መባሉ የጉጅሌው ቅጥረኛ የጸጥታ ሃይሎች ጽሁፎችን በማጥፋት ስራ ላይ መጠመዳቸውም የተዘገበው በዚሁ ባሳለፍነው ሳምንት ነበር። በአዲስ አበባ ጦር ሀይሎች፣ ወይራ ሠፈር፣ አዉጉሥታ፣ ቤቴል እና ሌሎችም አከባቢዎች የሙስሊሙን የመብት ጥያቄና የትግል ቀጣይነት የሚያንፀባርቁ ጽሁፎች በተለያዩ ቀለማት ተጽፈው ህዝብ ሲያነባቸው መታየቱን በስፋት መዘገቡ ይታወሳል። በአዲሳባና የክልል ዋና ከተሞች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተቃውሞ ጽሁፎችን ማየት የተለመደ እየሆነ መምጣቱን በተለያየ ጊዜ እየተከታተልን መዘገባችን ይታወሳል።

## ተዋርዶ መገዛት ይብቃን!

የወያኔ ሹማምንትና አደርባይ ሎሌዎቻቸው አንገቱን አስደፍተው የሚገዙትንና የሚዘርፉትን ህዝብ ይበልጥ ስብእናውን አዋርደው ሊገዙት ለምን እንደሚፈልጉ የማይገባን ጥቂቶች አይደለንም። እነዚህን ግፈኞች ቀረብ ብሎ ላያቸው ግን ይህ ድርጊታቸው እንቆቅልሽ አይደለም።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ህዝብ አይሰማንም ብለው በር ዘግተው ከሚያካሂዷቸው ጉባኤዎች እያፈተለኩ የሚወጡ የቪዲዮና የድምጽ መረጃዎች የነዚህን ግፈኞች ስነ ህሊና ግልጽ አድርገው ያሳያሉ።

ከወራት በፊት የሶማሊያ ክልል ፕሬዝዳንት የሀገር ሽማግሌ ሰብስቦ የወያኔ አላማ ከእሱ ጎሳ ጋር ተባብሮ ሌላውን ብሄረሰብ የበታች አድርጎ መግዛት መሆኑን ሲናገር የሚያሳይ ቪዲዮ ተመልክተን ነበር። የክልሉን ህዝብ የሚጨፈጭፈው ለዚህ ሲባል መሆኑን ለማሳመን ነበር በሩን ዘግቶ የተናገረው።
ሰሞኑን ደግሞ አንድ የአማራ ክልል የወያኔ ሹምና ሎሌ ልክ አንደ እንደ ሶማሌው ሹም ካድሬዎቹን ሰብስቦ በአማራው ህዝብ ላይ ተሳለቀ፤ ለ እግራቸው ጫማ የላቸውም በሚላቸው የአማራው ተወላጅ ላይ ለሰሚ በሚሰቀጥጥ ቋንቋ ያወርደው የነበረ ስድብ የሚነግረን ተጨማሪ ነገር ተመሳሳይ የወያኔን ምንነትን ነው።

እነዚህ ግፈኞች በህዝብ ላይ የሚሰሩትን አዋርዶ የመግዛት ግፍና ዝርፊያ አሳምረው ያውቃሉ። ከዚህ በላይ ደግሞ የዚህ ሁሉ ንቀትና ጥላቻ ሰለባ የሆነው ህዝብ እንደሚጠላቸውና ቀን እንደሚጠብቅላቸው ያውቃሉ። ስለዚህም ህዝቡን ይፈሩታል። ከፍርሃታቸው የሚያስታግስላቸው ህዝቡን ይበልጥ ቅስሙን ለመስበር ከቻሉ ስለሚመስላቸው በተዘጋ ቤት ውስጥ እየተሳለቁ ያስጨበጭባሉ።

የወያኔ ሹማምንት የህዝብ ብሶትና እሮሮ ማየሉን ሲሰሙ መልሰው ህዝቡን የሚሰድቡትና የሚያጠቁት፣ እንዲሁም ግንቦት 7 ሲጠነክርባቸውና የመውደቂያ ቀናቸው ሲያስቡ አሸባሪ ብለው የሚሸበሩትም ለዚህ ነው።

ህዝቡ ቅስሙ ከተሰበረ ሰላም ያገኙ ይመስላቸዋል። ወያኔዎችና የሲቪል ሰርቪስ ሎሌዎቻቸው በር ዘግተው በተሰበሰቡ ቁጥር ይህንን ፍራቻቸውን የሚያስታምሙት ህዝቡን ቅስሙን መስበራቸውን ለማረጋገጥ በሚያካሄዱት ወይይት ነው። ለዚህ ነው ህዝባችን እርስ በርሱ የሚባላበትን፤ እርስ በርሱ የጎሪጥ የሚተያይበትን መንገድ ሲቀይሱ የሚውሉት በዚህ ምክንያት ነው።

ወያኔዎች በየክልሉ እንደ አለምነው መኮነን አይነት ከጭንቅላታቸው፣ ከህሊናቸው ይልቅ አፋቸው የሚቀድም ጥራዝ ነጠቅ ሎሌዎችን የሚያሰማሩትም የህዝብን ቅስም የሰበሩ እየመስላቸዉ ነው።

ወያኔና ሎሌዎቹ ህዝብን የሚያታልሉበት ካርድ ከእንግዲህ አልቋል። አዋርደውናል፣ ገድለውናል፣ አስረውናል፣ አስርበውናል፣ ለስደት ዳርገዉናል፣ አለያይተውናል። ከዚህ በላይ ምን ሊያደርጉን ይችላሉ? ስለዚህ ቀኑ መሽቶባቸዋል እና በፍጥነት ሊወገዱ ይገባል።

በዚህ ወሳኝ ወቅት ሁሉም የኢትዮጵያዊ እንደ አንድ ህዝብ በአንድ ላይ በመነሳት የወያኔ ጉጅሌና አጎብጓቢ ሎሌዎቻቸው ያዘጋጁልንን ወጥመድ መስበርና ክብራችንን ማስመለስ ይኖርብናል። ሁሉም ኢትዮጵያዊ በተዘጋው የወያኔ በር እየተዋረደ፣ እየተገረፈ ነውና።

ግንቦት 7 እንደሁል ግዜው ዘላቂ መፍትሄ የሆነው ዴሞክራሲያዊ አንድነታችን እንዲጎለብት፣ ማንነታችን ክብራችን እንጂ መሳለቂያ እንዳይሆን በተባበረ ሃይላችን የክብራችን ባለቤት እንድንሆን ጥሪውን ያቀርባል።

በተባበረ ሃይላችን ክብረ-ስብእናችንን እናስመልስ! ተዋርዶ መኖር ይብቃን! በቃ!

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## "የወያኔ የእርቅ ጥያቄ ከተራ ፕሮፓጋንዳ ፍጆታ የዘለለ እርባና የለዉም "- ኢሳያስ አፈወርቂ

በቅርቡ ከኤርትራ ቴሌቪዥን ጋር ሰፊ ቃለ ምልልስ ያደረጉት የኤርትራ ፕሬዚዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ ከወያኔ ጋር ምንም ዓይነት የዕርቅ ፍላጐት እንደሌላቸው የወያኔ አገዛዝ ችግር ዉስጥ በገባ ቁጥር "የህዝብ ግንኙነት ብልጫ ለማግኘት እርቅ የሚባል ሃሳብ እየያዘ እንደሚመጣ ተናግረዋል። የኤርትራዉ ፕሬዚዳንት በሰጡት ሰፋ ያለ ምላሽ ምናልባት ቀደም ሲል ወያኔዎች እንዲህ ተባለ እንዲህ ሆነ እያሉ ሊያታልሉን ሞክረው ይሆናል፤ እኔ የሚገርመኝ ጊዜያቸውን በዚህ ለምን እንደሚያጠፉ ነው። የአዞ እምባ ነው። እኛን ሰይጣን እነሱን መልዓክ ለማስመሰል የሚደረግ ከንቱ ሙከራ ነዉ። እንደዚህ አይነቱን ተራ ነገር ባልሰማውና ባላስበው እመርጣለሁ። በአገር ውስጥም በውጭም ያለው የኤርትራ ሕዝብ ፈጽሞ ስለዚህ ማሰብ የለበትም፤» ብለዋል። ፕሬዚዳንቱ በዚሁ ምላሻቸው እየተባለ ያለው የዕርቅ ጥያቄ የውሸት መሆኑን፣ የኢትዮጵያ መንግሥት የፈጠራ ወሬ መሆኑንና ኤርትራዊያንን ለማሞኘት መሆኑን ይናገራሉ። በመጨረሻም ወያኔ ዕርቅ ለመፍጠር ‹ያላንኳኳው በር የለም› ካሉ በኋላ ዓላማው እውነት ዕርቅ ፍለጋ ሳይሆን ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ሰላም ወዳድ መስሎ ለመታየት ነው የሚል አስተያየት ሰጥተዋል።

"የተለያዩ ሚድያዎች ኢትዮጵያንና  ኤርትራን ለማቀራረብ የእርቅ ሙከራዎች እየተደረጉ ናቸው በማለት ዘግበዋል  ይህ ምን ያህል እውነት ነው? " በሚል ለቀረበላቸዉ ጥያቄ  በሰጡት ምላሽ በየጊዜው የሚናፈሰው የእርቅ ወሬ የወያኔ ምኞ ትና  ህልም እንጂ ምንም  መሰረት የሌለው ነው በማለት አጣጥለውታል።

"ወያኔ እስከምትጠፋ  ይህን ታስባለች። የህዝብ ግንኙነት ጠቀሜታ  ይገኝበታል ከሚል ፈሊጥ ነው ይህን የምታደርገው የምታወራው። የኮምሽኑን ውሳኔ ተቀብለናል ዲያሎግ ነው የምንፈልገው ሽምግሉን አስታርቁን እያለች ወያኔ ያላንኳኳቺው በር የለም። በአለም ላይ ያልተንኳኳ በር አለ ማለትአይቻልም። ይህ ሙዚቃዋ ሲደጋገም ሰልችቶናል። ድሮ በየዋህነት እንሳሳት ነበር። አሁን ግን ስለተደጋገመብን አንሳሳትም። አንዳንድ ግዜ  ለወያኔዎች በጣም ነው የማዝንላቸው። ለምንድን ነው ግዜያቸውን በከንቱ የሚያጠፉት ማንን ሊያሳስቱና ሊያደናግሩ ነው? ወያኔ አንዳንድ ግዜ  የአዞ  እንባ ታነባለች አንዳንዴ ትቆ ዝማለች። ይህ ሁሉ እኛን ሰይጣን ለማድረግ እራሷን መልአክ ለማስመሰል የምታደርገው ጥረት ነው። ስለዚህ በዚህ ጉዳይ ላይ በከንቱ ግዜያችንን ማጥፋት አይገባንም ።አንዳንድ ግዜ ይህ ጉዳይ ተስፋ አለው ብሎ ማሰብ ከያዝነው መስመር የሚያወጣን ስለሆነ ጆሮ ባንሰጠው ይሻላል። በውስጥና  በውጭ የሚገኙ ኤርትራውያን ማድመጥ ማሰብ የለባቸውም" በማለት መልስ ሰጥተዋል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የቀድሞው የአሜሪካ ስቴት ዲፓርትመንት አፍሪካ ጉዳይ ሃላፊ የሆኑት ሚስተር ሄርማን ኮህንና በኢትዮጵያ ቆይታቸው ከወያኔ ጋር የቅርብ ግንኙነት እንደነበራቸው የሚነገርላቸው  አምባሳደር  ደቪድ ሺን በየተራ" ኤርትራን ከብርዱ ወደ አለም አቀፉ ማህበረሰብ ማእቀፍ እንመልሳት በማለት የሰጡትን አስተያየት እንዴት እንዳገኙት የተጠየቁት ኢሳያስ አፈወርቂ፤ የሁለቱም የአሜሪካ ቀድሞ ባለሥልጣናት አነጋገርና የተጠቀሙት ቋንቋ ጭምር ለኤርትራ ህዝብ ስድብ እንደሆነ ገልጸዋል። "ኤርትራ አልበረዳትም የማንንም ብርድ ልብስ አትሻም" በማለት አስተያየታቸውን የገለጹት የ ኤርትራው ፕረዝዳንት "በኤርትራ ላይ ኢፍትሃዊ ማእቀብ ጥለው ህዝብ ካሰቃዩ  በኋላ ብርድና ሙቀት በሚል ቋንቋ ሊቀርቡን መፈለጋቸ ው አሳፋሪ ነው" በማለት ብዙ  የተባለለትንን የሁለቱን አሜሪካኖች መልእክት ትርጉም አሳጥተውታል።

ኢሳያስ አፈወርቂ ለአገራቸው ጋዜጠኞች የሰጡት ይህ ቃለ መጠይቅ በወያኔ በኩል እርቅ ሊመጣነ ነው እየተባለ በኦፊሲየልና  ኦፊሳልያዊ ባልሆነ  መንገድ የሚሰራጨውን ወሬ ፍሬ አልባነት ከማጋለጡም በላይ የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎችን መግቢያ መውጫ ለማሳጣት ይረዳኛል በማለት ወያኔ እርቅን ተስፋ በማድረግ የሚያደርገው እንቅስቃሴ እንዲገታ ቀዝቃዛ ወሃ የደፋበት መሆኑን ቃለመጠይቁን የተከታተሉት ሰዎችከሰጡት አስተያየት ለመረዳት ተችሎአል።

## ወያኔን ካላጠፋነዉ ዘረኝነቱና ዉርደቱ ይቀጥላል

ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች በራሳቸዉ እጅ የጻፉት ማኒፌስቶ በግልጽ እንደሚያሳየን እነዚህ ዘረኞች ጫካ ገብተዉ የትጥቅ ትግል እንዲጀምሩ ያነሳሳቸዉ በአማራ ህዝብ ላይ ያላቸዉ ጥላቻና መሰረተ ቢስ ቂም በቀል ነዉ። ይህ ጥላቻቸዉ ደግሞ አማራዉን በመግደልና ግዛቱን ሲያሻቸዉ ከራሳቸዉ ክልል ጋር በመቀላቀል አለዚያም ለጎረቤት አገሮች በመሸለም ብቻ ሊቆም ወይም ሊገታ አልቻለም። እነሆ የአማራው ህዝብ የወያኔ ዘረኞች ዋነኛ ዒላማ ሆኖ የአገዛዙን የግፍ ፅዋ ያለማቋረጥ መጋት ከጀመረ ድፍን 23 አመታት ተቆጠሩ። ፋሽስቱ ወያኔ የኢትዮጵያን ህዝብ ብሔራዊ ስሜት በማምከን ፣ የዘመናት ተገዥነቱን ለማረጋገጥ በቅድሚያ የአማራን ሕዝብ ማንነት ማጥፋት ፣ የአማራን ሕዝብ ስነ ልቦናዊ ጥንካሬ መስለብ እና አንገቱን ማስደፋት አስፈላጊ መሆኑን በጽናት ያምናል። ይህ በመሆኑም ፣ በአማራ ህዝብ ላይ በወያኔ የሚፈፀመው ግፍ እና በደል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ ስር እየሰደደና እየከፋ በግልፅም በስውርም በተቀነባበረ መንገድ ቀጥሏል።

ወያኔ የኢትዮጵያን ህዝብ ብሔራዊ ስሜት በማዳከም፣ ለዘመናት ሥልጣን ላይ ለመቆየት ያገለግለኛል ብሎ ዘመቻ ከከፈተባቸው ብሄረሰቦች አንዱና ዋንኛው የሆነው የአማራ ህዝብ በራሱ ማንነት እንዲያፍርና ብሄራዊ ኩራቱ እንዲሟሸሽ ላለፉት 23 አመታት በግብር ከፋዩ ህዝባችን ገንዘብ በሚተዳደሩ የመንግሥት መገናኛዎች ሳይቀር ከፍተኛ የስነ ልቦና ዘመቻ ተካሂዶበታል። በአማራ ሥም አማራውን የወያኔ አገር የማፍረስ አጀንዳ አስፈጻሚ ለማድረግ የተሾሙበት ተላላኪዎች በህወሃት አለቆቻቸው የተሰጣቸውን ተልዕኮ ለመፈጸም በተለያዩ አጋጣሚዎች አማራውን የሚያዋርድና የሚዘልፍ አስተያየት በአደባባይ ሲሰጡ ሰምተናል አይተናል። ይህ ተግባራቸው ለአማራ ህዝብ ቅንጣት ታህል ክብርና ፍቅር ያልነበረው ዘረኛው አለቃቸው መለስ ዜናዊ ከዚህች አለም በሞት ከተሰናበተ ቦኋላም ተጠናክሮ ቀጥሎአል።

የህወሃት መሪዎች አማራው ላይ ያላቸው ጥላቻ ወደሥልጣን ከመጡ ቦኋላ የተፈጠረ ሳይሆን ገና በጫካ ትግል ላይ በነበሩበት ወቅት በጻፉት የድርጅታቸው የፖለቲካ መረሃግብር በግልጽ እንደተቀመጠው ለትግል ያነሳሳቸውም አማራ ብለው የሚጠሩት ብሄረሰብ እንወክለዋለን በሚሉት ብሄረሰብ ላይ አድርሰዋል በሚሉት የፈጠራ በደልና ቂም እንደሆነ አረጋግጠዋል። ላለፉት 23 አመታት አማራው ከሚኖርበት የራሱ ክልሉ ሳይቀር እንዲፈናቀል ተደርጎ እየደረሰበት ያለው በደል የዚህ የቆየ የወያኔ ቂም በቀል ውጤት መሆኑ ግልጽ ነው።

ሰሞኑን  አለምነው መኮነን የተባለ ሆድ አደር  የባንዳነት ተግባሩን በመፈጸም በአለቆቹ ፊት ግርማ ሞገስ ለማግኘት  እመራዋለሁ የሚለውን የአማራ ህዝብ እጅግ በወረደና ጸያፍ በሆነ ቃላት ያን ያህል ሲዘባበትበት መደመጡ አማራውን ብቻ ሳይሆን መላውን የአገራችንን ህዝብ አስቆጥቶአል።

በእርግጥ አለምነው መኮንን አማራን በማዋረድ የመጀማሪያው የወያኔ ተላላኪ አይደለም። የህወሃቶቹን ቁንጮዎች ስድብና ዘለፋ ወደ ጎን ትተን በወያኔ የዘር ፖለቲካ አማራውን እወክለዋለው የሚለው ብአዴን ከፍተኛ አመራር እነ እነታምራት ላይኔ ተፈራ ዋልዋና በረከት ስምን በተለያየ ወቅት ንቀትና ስድባቸውን አሰምተውናል። አለምነህ መኮንን እንደዚያ በወረደ ቃላት አማራውን ሲያዋርድ በስብሰባው አዳራሽ የነበሩ ህወሃት የፈጠራቸው የብአዴን ልጆች በሳቅ ካካታ ሲያጅቡት እንደነበረ እድሜ ለኢትዮጵያ ሳታላይት ቴለቪዥን ከአዳራሹ ሾልኮ ለህዝብ ጆሮ የደረሰው የኦዲዮ ድምጽ አጋልጦአል።

ሁላችንም፤ እንደምንገነዘበው ወያኔ የገዛ ብሄረሰባቸውን ረግጠው በመግዛት የጥፋት አላማውን እንዲያስፈጽሙለት በራሱ አምሳል ከፈጠራቸው ድርጅቶች አንዱ የሆነው ብአዴን በታሪኩ አንድም ለህዝቡ የቆመ መሪ አፍርቶ አያውቅም። ለራሳቸውና ከአብራኩ ለተገኙት ህዝብ ምንም አይነት ክብር የሌላቸው የብአዴን መሪዎች  ጣሊያን አገራችንን በወረረችበት ወቅት ለሆዳቸው ሲሉ ከባዕድ ጋር ተሻርከው ህዝባቸውን ካስጨፈጨፉት ባንዳዎች የከፋ ተግባር በህዝባቸው ላይ እየፈጸሙ ነው።

ወያኔ ለም የሆነውን የአማራ ግዛት እንዳለ የኔ ነው ወደሚለው የትግራይ ክልል ሲወስድ፤ በአማር ክልል ወስጥ በቀሩት ለም ቦታዎች የህወሃት ታማኝ ካድሬዎችን ከያሉበት እያጓጉዘ ሲያሰፍር፤ የአገሬውን አርሶ አደር እያፈናቀለ ለራሱ ታማኞች ለም መሬት እየሸነሸነ ለሰፋፊ እርሻ አገልግሎት ሲያድል አማራውን እወክለዋለው የሚለው ብአዴን አንድም የተቃውሞ ድምጽ አሰምቶ አያውቅም። የብአዴን መሪዎች የወያኔን ተልዕኮ ከማስፈጸም አልፈው በሟቹ አለቃቸው በመለስ ዜናዊ ሥም እየማሉ በአገራችን ኢትዮጵያና በሚያስተዳድሩት የአማራ ህዝብና ክልል የሚፈጽሙት በደል ብዙ ነው። ልክ እንደ ብአዴን የዘረኛውን  ወያኔ የጥፋት ፖሊሲ ለማስፈጸም ከሚተጉት አንዳንዶቹ አማራውን ከክልላቸው ለማጽዳት በቤኒሻንጉል፤ በቤንች ማጅና ጉራፈርዳ ወረዳ እርምጃ ሲወስዱና ንብረታቸውን ቀምተው ባዶ እጃቸውን ሲያባርሩዋቸው ብአዴን ቁጭ ብሎ ተመልካች ነበር። ከአማራ ክልል ጋር የሚዋሰነው ዳር ድንበራችን ላይ በተነሳው የባለቤትነት ጥያቄም ላይ የወሰደው አቋም በህዝብና በታሪክ ፊት ውሎ አድሮ የሚያስጠይቀው ነው።

እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ እንደሚገነዘበው ፋሽስቱ ወያኔ በአገራችንና በህዝባችን  ላይ እየፈጸመው ያለው አንዱን ዘር ከሌላው ጋር የማጋጨትና በተናጠል ደግሞ እያንዳንዱን ለይቶ የማዋረድና የማጥፋት ተግባር አሁን የተጀመረ ክስተት አይደለም። የቆየና ወያኔ ህዝባችንን ከፋፍሎ ለመግዛት ከመነሻው ሲጠቀምበት የነበረ ስልት ነው። ስለዚህ ወያኔ በራሱና በተላላኪዎቹ አማካይነት ላለፉት 23 አመታት በህዝባችን ላይ እየፈጸመ ያለውና የፈጸመው ግፍ፤ ውርደትና መከራ እንዲያበቃ ሁላችንም እጅ ለ እጅ ተያይዘን መነሳት ይኖርብናል። በወያኔ ከፋፋይ አጀንዳ እርስ በርስ እየተናቆርን የጥቃት ሰለባ የመሆናችንን እንቆቅልሽ ለማስቀረት ከኛ በላይ ሃይል ያለው አይኖርም።

በተለይ ግንባር ቀደም የወያኔ ሰለባ የሆነው የአማራ ህዝብ ወጣት በጫንቃው ላይ ተፈናጠጠው የወያኔን የጥላቻና የበቀል እርምጃ የሚያስፈጽሙትን ከአብራኩ የተገኙ ባንዳዎች ላይ የጥቃት ክንዱን መሰንዘርና ለክብሩ መቆሙን ማሳየት ያለበት ጊዜው አሁን ነው።

በብአዴን ሥር የተሰባሰቡ የአማራ ተወላጆች፤ በመከላኪያ ሠራዊቱ፤ በፖሊስና በደህንነት፤ በወጣት ማህበር፤ በሠራተኛ ማህበርና በተለያየ ሙያ ማህበር ብአዴን ራሱ ያደራጃቸው ሁሉ ለክብራቸውና ለኢትዮጵያዊ ማንነታቸው ሲሉ ከትግሉ ጎን በመሰለፍ የወያኔን ዕድሜ ለማሳጠር ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የሚያካሂደውን ትግል እንዲቀላቀሉ ንቅናቄው ጥሪውን ያቀርባል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## ለሙስና የተጋለጠዉ ቡና ኤክስፖርት ድርጅት የወያኔ ባለስልጣኖችን ኪስ እየሞላ ነዉ

ቡናን ወደ ዉጭ ገበያ ከማቅረብ ስራ ጋር የተያያዙት የቁጥጥርና ክትትል ስራዎች፤ መረጃ አያያዝና እንዲሁም የመጋዘኖች ቆጠራና ጥበቃ ሆን ተብሎ እንዲረሳ በመደረጉ ኢትዮጵያ ከቡና ንግድ ማግኘት የነበረባት ከፍተኛ ቁጥር ያለዉ የዉጭ ምንዛሪ ወደ ወያኔ ባለስልጣኖች ኪስ እንደሚገባ አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ የግንቦት ሰባት ድምጽ ዘጋቢዎች በላኩልን ዜና ገለጹ። ወያኔ እራሱ ያቋቋመዉ የፀረ ሙስና ኮሚሺን አንዳንድ የወያኔ ባለስልጣኖች ያለብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ቡናን ወደውጭ እንደሚልኩ የበቅርቡ ለህትመት የበቃዉ አንድ የኮሚሺኑ ጣናታዊ ሪፖርት አጋልጧል።

ጥናቱ ኤክስፖርት በማያደርጉ ድርጅቶች ላይ እርምጃ ያለመውሰድ፣ በንግድ ፈቃድ ላይ የተጠናከረ ቁጥጥር ያለማድረግ እና በሕገወጥ የቡና ምርት ዝውውርና ግብይት ላይ የሚመለከታቸው አካላት ተቀናጅተው ያለመስራት በዘርፉ የሚታዩ ችግሮች መሆናቸውን ማመላከቱን ኮምሽኑ በድረገጹ ላይ ባሰፈረው ዜና ገልጿል።ኢትዮጵያ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ከምታገኝባቸው የግብርና ምርቶች መካከል በቀዳሚነት የሚጠቀሰው የቡና ኤክስፖርት ሒደት ለሙስናና ብልሹ አሠራር ያለውን ተጋላጭነት አስመልክቶ በኮሚሽኑ የተካሔደው ጥናት ይፋ የሆነው ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት በተገኙበት ሰሞኑን በግዮን ሆቴል ጥናቱን ለማዳበር በተከናወነ የምክክር ስብሰባ ላይ ነው። የውይይት መድረኩ የተዘጋጀበት ዓላማ በዘርፉ ስለሚስተዋሉ የአሠራር ጉድለቶች ለሚመለከታቸው ክፍሎች ግልጽ ግንዛቤ ለማስያዝና ችግሮቹን በመቅረፍ ረገድ የተሻለ አሠራር በማመላከት የመፍትሔው አካል ሆነው የድርሻቸውን እንዲወጡ ለማስቻል እንዲሁም በክፍተቶቹ ዙሪያ የጋራ ግንዛቤ በመያዝ ለመፍትሔው በጋራ ለመንቀሳቀስ ነው ተብሎአል።

.........................................................................................................

## የወር ደሞዛቸዉ ከ500 ብር የማይበልጠዉ የህወሃት ታጋዮች በሚሊዮን የሚቆጠር ንብረት እንዳላቸዉ ታወቀ

በሙስና ወንጀል ተከስሶ ፍርድ ቤት ከቀረበዉ ከወያኔዉ የደህንነት ሃላፊ ወልደስላሴ ወልደ ሚካኤል ጋር በግብረ-አበርነት የተከሰሱት የህወሃት ታጋዮች ከደሞዛቸው ጋር ፈጽሞ የማይመጣጠን ሃብት አግበሰው መገኘታቸው ተጋለጠ። ከመለስ ዜናዊ ሞት በኋላ በህወሀት ዉስጥ በተፈጠረዉ የርስበርስ ሽኩቻ የተነሳ አንዱ ወያኔ ሌላዉን ወያኔ መክሰስ መጀመሩ የህወሃት ተጋዮች በህገወጥ መንገድ የሰበሰቡትን የሃብት መጠን ለማወቅ እየረዳ መሆኑን ብዙዎች ይስማሙበታል። ለምሳሌ ከአቶ ወልደስላሴ ጋር በግብረ አበርነት የተከሰሱት የቀድሞዉ የህወሃት ታጋይ የአቶ ወልደስላሴ ወንድም አቶ ዘርአይ ወልደስላሴ ከመከላከያ ሚኒስቴርን ሲሰናበት ይከፈለዉ የነበረው ወርሃዊ ደሞዝ 532 ብር ብቻ እንደነበር አመልክቷል። ይሁንና፣ ጸረ-ሙስና ኮሚሽን ባደረገው ማጣራት ግለሰቡ በተለያዩ ባንኮች በስሙ 5 ሚሊዮን ብር ከማስቀመጡ በተጨማሪ፣ አዲስ አበባ ቤቴል ሆስፒታል አካባቢ በ74 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ግንባታ እያካሄደ፣ በአፋር ክልል ደግሞ ከ1 ሚሊዮን 400 መቶ ሽ ብር በላይ በሆነ ወጪ የእርሻ ኢንቨስትምንት እያከናወኑ መሆናቸው እንዲሁም በስማቸው 2 ሚሊዮን 700 ሺ ብር ግምት ያላቸው 2 ሎደር መኪኖች መገኘታቸውን ገልጽዋል።

የአቶ ወልደስላሴ እህት የሆኑት ወ/ሮ ትርሃስ ደግሞ የ8ኛ ክፍል ተማሪና ምንም ስራ ያልበራቸው ሲሆን፣ በወንድሞቻቸው ድጋፍ ከ2 ሚሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ የተገዛ አንድ ስካቫተር፣መኪና እንዲሁም በአዲስ አበባ በየካና ቦሌ ክፍለ ከተሞች፣ በለገጣፎ፣ መቀሌና አክሱም 3 ሺ 266 ካሬ ሜትር ቦታዎች በስማቸው መገኘቱ ተመልክታል ፣እንዲሁም በተለያዩ ባንኮችም 8 ሚሊዮን ብር ተቀማጭ ማድረጋቸውን አንድ ተጨማሪ ዘመናዊ መኪና በስማቸው ተመዝግቦ መገኘቱን ጸረ ሙስና ኮሚሽን በምርመራ አረጋግጧል። ዋናው ባለስልጣን አቶ ወልደስላሴ ደግሞ ስራ ሲጀምሩ ደሞዛቸው 1600 ብር የነበረ እና በእድገት እስከ 6000 ሺ ብር ሲከፈላቸው የቆየ ቢሆንም ያካባቱት ሀብት ግን ፈጽሞ ከደሞዛቸው ጋር የማይመጣጠን ነው ተብሏል። ባለ 4 ፎቅ ህንጻ ባለቤት የሆኑት አቶ ወልደስላሴ በ1 አመት ከ2 ወራት ቤቱን አከራይተው 790 ሺ ብር ገቢ አግኝተዋል።

አቃቢ ህግ ያቀረበውን ክስ የእስረኞች ጠበቆች፣ አዲስ የተጨመረ ክስ ነው በማለት አቤቱታ አቅርበዋል።አቶ ወልደስላሴ ከወ/ሮ አዜብ ጋር በነበራቸው መቀራረብ ከፍተኛ ሃብት ማፍራታቸውን ፤ አቶ መለስ ዜናዊ ከሞቱ በሁዋላ ግን የእርሳቸው ዋነኛ ተቀናቃኝ የሆኑት የደህንነቱ ዋና አዛዥ አቶ ጌታቸው አሰፋ ግለሰቡን በሙስና ከሰው እንዳሳሰሩዋቸው አንዳንድ የመገናኛ ብዙሀን ገልጸው ሲዘግቡ ቆይተዋል። ህወሃቶች እርስ በርስ በሚያደርጉት ሽኩቻ እየተካሰሱ ፍርድ ቤት መቅረባቸው የካበቱትን ሃብት ለማወቅ እየረዳ ነው የሚለው ዘጋቢያችን፣ በጸረ ሙስና ኮሚሽን ያልተመረመረና በፍርድ ቤት ቀርቦ ያልታወቀ ከዚህም የባሰ የሙስና ታሪክ እንደሚኖር መገመት ይቻላል ሲል አስተያየቱን አስፍሯል።

## ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ለሱዳን የተሰጠ መሬት የለም ፤መሬት የምንሰጥበት ምክንያትም የለም አለ

የወያኔዉ ጠ/ሚኒስትር ኃ/ማሪያም ዳሳለኝ በቅርቡ ለጋዜጠኞች በሰጠዉ መግለጫ የኢትዮጵያ መንግስት ለሱዳን የሚሰጠዉ ምንም መሬት የለም፤ መሬት የሚሰጥበት ምክንያትም የለም ብሎ መናገሩ ከቀርብ ግዜ ወዲህ አወዛጋቢ እየሆነ የመጣዉን የኢትዮጵያንና የሱዳንን ድንበር ጉዳይ በቅርብ የሚከታተሉ አያሌ ኢትዮጵያዉያንን እያናገረ ነዉ። በቅርቡ ካርቱም ዉስጥ የተደረገዉን የሁለቱን መንግስታት ስብሰባ አስመለክቶ በሰጠዉ መግለጫ በሱዳንና በኢትዮጵያ መንግሥታት መካከል በየሁለት ዓመቱ የሚደረግ የጋራ ኮሚሽን ስብሰባ አለን። ይህ ቋሚና በየሁለት ዓመት በሁለቱ መንግሥታት መካከል የሚደረግ የኮሚሽን ስብሰባ ነው። ይህ የኢትዮጵያና የሱዳን ድንበርን በተመለከተ በቀጥታ የሚካሄድ ስብሰባ አይደለም። ይህ ስብሰባ በኢኮኖሚያዊ፣ በፖለቲካዊ፣ በማኅበራዊ፣ በአኅጉራዊና በዓለም አቀፋዊ ጉዳዮች ውይይት የሚደረግበት ነው። ይህ የድንበር ጉዳይ በዚህ ስብሰባ ላይ በተደጋጋሚ የሚነሳ አጀንዳ ነው። የተለየ ነገር በዚህ ስብሰባ ላይ ተነስቶ የወሰነው ነገር የለም በማለት ስብሰባዉ የኤኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳዮች ስብሰባ እንደሆነ ለመናገር ሞክሯል።

የተሸከመዉን የጠ/ሚኒስቴርነት ቦታ የሚመጥን የፖለቲካ ኃይል የሌለዉና በል ያሉትን ብቻ በየተገኘበት ቦታ ሁሉ እየሄደ የሚናገረዉ ኃ/ማሪያም ዳሳለኝ ለሱዳን መሬት ሊሰጥ ነዉ እየተባለ የሚነሳዉ ጥያቄ ከምርጫ ጋር ተያይዞ በየአምስት አመቱ የሚነሳ ጥያቄ ነዉ በማለት የወያኔን ተራ የማጭበርበሪያ ምርጫ የአገሪቱን ዜጎች በያሉበት እጅግ በጣም ከሚያሳስባቸዉ ከድንበር ጥያቄ ጋር ለማገናኘት ሞክሯል። በጋዜጣዊዉ ጥያቄና መልስ ወቀት ጠ/ሚኒስቴር ተብዬዉ እንዲህ ነበር ያለዉ - እንደምታስታውሱት በ2001 ዓ.ም. መጨረሻ አካባቢ የኢትዮጵያና የሱዳን ድንበር ጉዳይ በተመሳሳይ መልኩ ተነስቶ ነበር። በወቅቱም የድንበር ማካለል አለመካሄዱን፣ የሁለቱ መንግሥታት የድንበር ጉዳይ ታሪካዊ ሁኔታው፣ እንዲሁም አሁን የደረሰበት ደረጃ በዝርዝር የተተነተነበት መግለጫ ተሰጥቷል። ይህ መግለጫ የተሰጠው በ2001 ዓ.ም. ነው፣ 2001 ዓ.ም. ማለት ከዛሬ አምስት ዓመትሱዳ በፊት ነው። በተመሳሳይ መንገድ በ1996 ዓ.ም. ተመሳሳይ ጥያቄ ተነስቷል። ከ2001 ዓ.ም. ላይ አምስት ዓመት ብንቀንስ 1996 ዓ.ም. ነው። ስለዚህ በ1996 ዓ.ም. ጥያቄው ተነስቶ መልስ ተሰጥቶበታል። በ2001 ዓ.ም. ተነስቶ መልስ ተሰጥቶበታል።

አሁን ደግሞ በ2006 ዓ.ም. ከአምስት ዓመት በኋላ ጥያቄው ተነስቷል መልስ እንሰጥበታለን። መልሱ ግን አንድ ዓይነትና ተመሳሳይ ነው። ጋዜጣዊ መግለጫዉንና ይህንን በድንበር ጉዳዮች ላይ የተሰጠዉን መልስ አስመልክተን አገር ቤት በስልክ ያናገርናዉቸዉ ብዙ ሰዎች የኃ/ማሪያምን ንግግር ተራና ምንም አይነት ፖለቲካዊ ብስለት ያልታከለበት እንኳን ኢትዮጵያን ያክል ትልቅ አገር ከሚመራ ሰዉ ከተራ ሰዉም የማይጠበቅ ተራ ንግግር ነዉ ብለዋል።አንዲት ስሟ እንዳይጠቀስ የፈለገች የአዳማ ዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ አመት ተማሪ ኃ/ማሪያም የወያኔ ተላላኪ ነዉ፤ የሚናገረዉም እነሱ ተናገር ያሉትን ብቻ ነዉ። አንድ ጥያቄ ያዉም የአገርን ድንበር ያክል የተከታታይ ትዉልድ በተከታታይ የሚነሳዉ ህዝብ ለጥያቄዉ አግባብ ያለዉ ትክክለኛ መልስ ስላልተሰጠዉ ነዉ እንጂ ጥያቄዉ ምርጫ ስለደረሰ ብቻ የሚነሳ ጥያቄ አይደለም። ደግሞስ ወያኔ ከራሱ ጋር ተወዳድሮ አሸንፍኩ ለሚለዉ ምርጫ ማን ተጨንቆ ነዉ ማዘናግያ ነገር እየያዘ በያምስት አመቱ የሚመጣዉ? ይልቅ ጥያቄዉ በተነሳ ቁጥር አንድ አይነት መልስ ከመመለስ ጥያቄዉን የሚመጥን ትክክለኛ መልስ ለመመለስ ሞክር ስትል በሳል አስተያየት ሰጥታለች።

## ግብፅና ኢትዮጵያ በአባይ ወንዝ ጉዳይ የሚያደርጉት ውይይት እንደገና ተቋረጠ-

በግብፅ የውኃና መስኖ ሚኒስትር መሐመድ አብዱል ሙታሊብና በኢትዮጵያዊዉ አቻቸው አቶ አለማየሁ ተገኑ መካከል ባለፈው ሰኞ አዲስ አበባ ይደረጋል ተብሎ ሲጠበቅ የነበረዉ የሁለትዮሽ ዉይይት ስብሰባዉ በተጀመረ በሰአታት ዉስጥ መቋረጡን አገር ዉስጥ የሚታተሙ የተለያዩ ጋዜጦች ዘገቡ። ለምሳሌ በሩፖርተረ ዘገባ መሰረት የግብፅ ሚኒስትር ከኢትዮጵያ አቻቸው አቶ አለማየሁ ተገኑና ከባልደረቦቻቸው፣ እንዲሁም ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከተወከሉ ባለሙያዎች ጋር ባለፈው ሰኞ ተገናኝተዋል። ሀኖም ግብፃዉያኑ ይዘዉት የመጡት አጀንዳዎችም ከዚህ ቀደም ተቀባይነት ያላገኙና የዓለም አቀፍ ባለሙያዎች ቡድን ተጨማሪ ጥናት እንዲያከናውን የሚጠይቁ አጀንዳዎች በመሆናቸዉ ዉይይቱ እንደተጀመረ ወድያዉ ሊቋረጥ ችሏል።

በግድቡ ግንባታ ላይ መተማመንን ማጐልበት በሚል በግብፅ በኩል በቀረበው ሐሳብ ውስጥ የቀድሞው የግብፅ የውኃ መጠን እንደማይቀንስ ኢትዮጵያ እንድታረጋግጥ የሚጠይቅ ነው።ይህንን በተመለከተ በሰኞው ስብሰባ የግብፁ ሚኒስትር በድጋሚ አንስተው ኢትዮጵያ እንደማትቀበለው ግልጽ እንደተደረገላቸው አቶ አለማየሁ በውይይት መድረኩ ላይ ለተገኙ ጋዜጠኞች ገልጸዋል። ባለሙያዎች ያቀረቧቸው ምክረ ሐሳቦች ተግባራዊ እንዲደረጉ፣ የግድቡ ግንባታ ይቁም ብለው መጠየቃቸውን አቶ አለማየሁ ተገኑ ገልጸዉ አግብዖች ያነሷቸው ጥያቄዎች በጭራሽ በኢትዮጵያ በኩል ተቀባይነት እንደማይኖራቸውና የግድቡ ግንባታም ለሰከንዶች እንደማይቆም ካስረዳናቸው በኋላ ምሳ ጋብዘናቸው በሦስት ሰዓታት ውስጥ ተለያይተናል፤» ሲሉ አቶ አለማየሁ ተናግረዋል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## የጋዜጠኛው ጥያቄ ጠ/ሚኒስትሩን አስቆጣ

የወያኔዉ ጠ/ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ ባለፈዉ ሳምንት ለአገር ውስጥ ጋዜጠኞች በሰጠዉ ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ከፎርቹን ጋዜጣ ዘጋቢ ከአቶ ታምራት ገብረጊዮርጊስ የቀረበለትን ጥያቄ በአግባብ መመለስ ተስኖት ዘለፋ የተቀላቀለበት የቁጣ መልስ መልስ መመለሱን ከአገር ቤት የደረሰን ዜና አስረዳ። ለወትሮዉ በተለይም ከቀድሞዉ ጠ/ሚኒስቴር ጋር ሲነጻጸር አንደበተ ሽጋ ነዉ እየተባለ ይነገርለት የነበረዉ ኃ/ማሪያም ቀላልና ግልጽ ጥያቄ መመለስ ተስኖት ቁጣና ተራ ስድብ ላይ ሲያተኩር ተስተዉሏል።

አቶ ታምራት ለጠ/ሚኒስትሩ ያቀረቡት ጥያቄ በአሁን ሰዓት አገሪትዋን የሚመራት ማንነው ነው የሚል ይዘት ያለው ሲሆን ጠ/ሚኒስትሩም ብስጭታቸውን በምላሻቸው ወቅት አንጸባርቀዋል። ጠ/ሚኒስትሩ ለዚህ ጥያቄ ቀጥተኛ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ ጋዜጠኛውን ሂድና እዚያ ሐሜት የምትጽፍበት ገጽ ላይ ጻፈው በማለት መዝለፋቸው በርካታ ጋዜጠኞችን አስደንግጦአል። አንዳንድ ጋዜጠኞች ስለሁኔታው በሰጡት አስተያየት ጋዜጠኛ ታምራትን በማድነቅ አንድ ጋዜጠኛ በሕዝብ ውስጥ የሚነገርን ጥያቄ አውጥቶ መጠየቁ ተገቢና ሙያዊ ሃላፊነቱ መሆኑን በመጥቀስ ጠ/ሚኒስትሩ ጥያቄው የቱንም ያህል ቢያበሳጫቸው በዚህ መልኩ ምላሽ መስጠታቸው ራሳቸውን ከማስገመት ያለፈ ትርፍ እንደሌለው ተናግረዋል።

ከአቶ መለስ ሞት በሃላ ወደስልጣን የመጡት አቶ ኃይለማርያም ቀደም ሲል በአቶ መለስ ብቻ ሲመራ የነበረውን የጠ/ሚኒስትር ስልጣን የጋራ አመራር በሚል ፈሊጥ ሶስት ቦታዎች በመክፈልና በምክትል ጠ/ሚኒስትር ማዕረግ ለኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ስልጣናቸው ማከፋፈላቸው በሕዝብ ዘንድ ያለስልጣን የተቀመጡ አሻንጉሊት መሪ እስከመባል አድርሶአቸዋል።ጠ/ሚኒስትሩ በዚሁ መግለጫቸው ብዙ ሲባልበት የቆየውን ኢትዮ ሱዳን ድንበር ማካለል ጉዳይ ከውይይት ያለፈ ነገር እንደሌለ በመናገር የሚደርስባቸውን ትችቶች ያጣጣሉ ሲሆን አጀንዳውንም ከመጪው ምርጫ ጋር በማያያዝ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት የሚደረግ ሙከራ መሆኑን ለመናገር ሞክረዋል። በኢትዮ ሱዳን ድንበር ማካለል ጉዳይ በስፋት የዘገቡትና ሒደቱንም ያሳወቁት የሱዳን ጋዜጦች መሆናቸውን በተመለከተ ያሉት ነገር የለም። ከኢህአዴግ ጋር በመደራደር አገር ውስጥ ገብተዋል ስለተባሉትም አቶ ሌንጮ ለታ ተጠይቀው ዋሽንግተን ለሚገኘው ኢትዮጵያ ኤምባሲ ደብዳቤ ማስገባታቸውን ከመስማታቸው ውጪ ስለመግባታቸው የሚያውቁት ነገር እንደሌለ በመናገር ጉዳዩን አስተባብለዋል።

## የፍትህን በር እየዘጉ ስለፍትህ ማዉራት

. . . ( ከገጽ 3 የዞረ )

ባደባባይ መናገር ከውርደትም በታች መውረድ ነው የሚሉት ታዛቢዎች፤ አምባገነን የነበረው ደርግ እንኳ በዚህ መልኩ ወርዶ ራሱን ባደባባይ ሲያጋልጥ አልታየም ያላሉ።

ህግ አውጭው የተባለውን ብቻ እንጅ ሀገራችንና ሕዝባችን የሚያስፈልጋቸውን ህጎች እንዳያጸድቅ በሚታዘዝበት፣ ሰዎች ከታሰሩ በኋላ ለእስራቸው የሚጠየቁበት ህግ በሚወበት፣ ህግ ተርጓሚው በፋሽስት ወያኔ እየተመራ በሚፈርድበትና በስህተት ሕወሃት ያልፈለገው ውሳኔ ከተላለፈ እንኳ በፋሽስት ወያኔ ቀጥተኛ ጣልቃ ገብነት ውሳኔው በሚሻርባት ኢትኦጵያ "እድገታችንን ቀጣይ የሚያደርገው ፍጹም ያልታየው የወያኔ የፍትህ ስርአት ጠንክሮ ሲወጣ ነው" እያሉ በሌለ ነገር ላይ ብዙ ማውራት ሃይለማሪያም ደሳለኝም ሆነ ሕወሃት እንመራዋለን ከሚሉት ሕዝብ ምን ያህል ርቀው እንዳሉ ሚያሳይ ነው የሚሉ ብዙዎች ናቸው።

ፋሽስት ወያኔ ከዚህ በፊት በግንቦት 7 እና በሃይማኖት አክራሪነት ስም ተፈርጀው በሽብርተኝነት የተከሰሱ ብዙ ወገኖቻችን ከወያኔው ፍርድ ቤት ውጭ በአስገዳጅነት የተናገሩትን በመመዝገብና ቃላችን ነው ብላችሁ ፈርማችኋል በማለት ከፍተኛ የጥፋተኝነት ውሳኔ ሲያስተላልፉባቸው እና ለጥፋተኝነታቸው ማስረጃ አደርጎ ሲያቀርብ እንደነበር ይታወሳል።

## ወያኔ ለራሱ ለሚገነባዉ የባቡር መስመር በኢትዮጵያ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በእስካሁኑ ጉዞው በርካታ ቢሊየን ዶላሮችን በልማት ስም ከተለያዩ የአለማቀፍ ተቋማት በመበደር በጉጅሌው ሙሰኛ ባለስልጣናት እየተመዘበረና ልማት ተብለው የሚጀመሩት ስራዎች ሁሉ በእንጥልጥል ለብልሽትና ለኪሳራ እየተዳረጉ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን፡ የልማት ተብየ ስራዎችም ሃገርና ወገንን ከመጥቀም ይልቅ የባዕዳንን ኪስ እየሞሉ ያሉ መሆናቸው የሚታወቅ ነው። ለአብነትም በቅርቡ ካሪቶሪ ከተሰኘው የህንድ ኩባንያ ጋር የተፈጠሩ አለመግባባቶችን መመልከት ይቻላል። ፋሽስቱ ወያኔ የመጭውን ትውልድ በዕዳ ዘፍቆ ለማለፍ ታጥቆ የተነሳ የሌባ ስብስብ ስለመሆኑ በርካታ ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ይስማማሉ። በጉዳይ ዙሪያ በርካት ያሉ የህዝብ አስተያየቶችን አሰባስበን በቅርቡ ይዘን እንደምንመለስ በዚህ አጋጣሚ ለማስታወስ እንወዳለን።

## የህወሃት ታጋዮች አርስ በርሳቸዉ እየተሿከቱ የሀገሪቱን ሀብትና . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

የወልደስላሴ እህት ስሟ ትርሃስ ትባላለች፡ የ8ኛ ክፍል ተማሪና ምንም ስራ ያልነበራት ሲሆን፣ በወንድሞቿ ድጋፍ ከ2 ሚሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ የተገዛ አንድ ስካቫተር መኪና እንዲሁም በአዲስ አበባ በየካና ቦሌ ክፍለ ከተሞች፣ በለገጣፎ፣ መቀሌና አክሱም 3 ሺ 266 ካሬ ሜትር ቦታዎች በስሟ መገኘቱ የተመለከተ ሲሆን፣ በተለያዩ ባንኮችም 8 ሚሊዮን ብር ተቀማጭ ማድረጓን፡ አንድ ተጨማሪ ዘመናዊ መኪና በስሟ ተመዝግቦ መገኘቱን ጸረ ሙስና ኮሚሽን በምርመራ አረጋግጧል።

የደህንነት ሃላፊ ከነበረው ዋናው ተከሳሽ ወልደስላሴ ወልደ ሚካኤል ስራ ሲጀምር ደሞዙ 1600 ብር የነበረ እና በእድገት እስከ 6000 ሺ ብር ሲከፈለው የቆየ ቢሆንም ያካባተው ሀብት ግን ፈጽሞ ከደሞዙ ጋር የማይመጣጠን ነው ተብሏል። ባለ 4 ፎቅ ህንጻ ባለቤት የሆነው ወልደስላሴ በ1 አመት ከ2 ወራት ቤቱን አከራይቶ 790 ሺ ብር ገቢ አግኝቷዋል። 90 ሚሊዮን ህዝብ በርሃብና በችግር የዕለት ኑሮውን በሚገፋባት ኢትዮጵያ ጥቂት የጉጅሌው መስራች የህውሃቶች በዝርፊያ ባካበቱት ገንዘብ ከአፍሪካ በሃብት ደረጃ ተወዳዳሪ የሌላቸው መሆናቸውን በርካታ የአለም አቀፍ የዜና አውታሮች በሚያወጡት ሪፖርት በተደጋጋሚ መዘገቡ ይታወቃል።

## የህወሃት ታጋዮች አርስ በርሳቸዉ እየተሿከቱ የሀገሪቱን ሀብትና . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

## የወያኔ ሴራ

ከመቃብር ምሶ፣
ሙታንን ቀስቅሶ፣
ዘር አጥንት ቆጥሮ ከሰውነት ወጥቶ
እንደራበው ውሻ አጥንት እየጋጠ፣
በስንቱ ቀለደ በስንቱ አላገጠ።

ዛሬን እንዳንቃኝ እንዳናልም ነገን፣
ሁል ጊዜ በፍርሀት እያሸማቀቀን፣
ሽብረተኛ እያለ ሽብር ሲዘራብን፣
እኛም ሚስኪን ህዝቦች እንቀበላለን።

በጥላቻ ወሬ እግር ከወርች ታስረን፣
እንዳንከባበር በትዕቢት ተውጠን፣
አንዱ አንዱን ላይሰማው ስንደነቁዋቆር
ሁሉም በያለበት እየየውን ሲያወርድ፣
የተጫነብንን መርገም እንደማውረድ፣
አንድ መቶ ዓመታት የሁዋሊት ተጉዘን፣
ከሙታን መንፈስ ጋር እንፋለማለን።

ሀገርን ባቀና ክብርን ባስመለሰ፣
የምኒልክ ሐውልት ይላል ካልፈረሰ።
ወያኔ የሚባል የባንዳ ስብሰብ፣
ከከርሱ ውጪ ምንም የማያስብ፣
መርዝ እንደቀመመ ተንኮል እንዳደራ፣
በጅምላ እንዳሰረ ካገር እንዳስወጣ፣
ሌላ ማዘናጊያ አኖሌ 'ሚል መጣ።

ስንት ሰዎች አለን ግራ የተጋባን፣
የሰጡንን ስራ ሰርተን ያልጨረስን።
አንዴ አብዮታዊ ሲለው ልማታዊ፣
ፌደራልም አልከው ወይም ክልላዊ፣
በቃላት ጋጋታ ህዝብን እያምታታ
መልክ እና ጸባዩን እየለዋወጠ
ሥልጣን ኮርቻ ላይ ከተቆናጠጠ

ዘመናት ነጎዱ
ስንት ኹነት ሄደ ስንት ኹነት መጣ
ወገኔ ከችርግ ከዋይታ ሳይወጣ።

አንዱዓለም፣ ውብሸት፣
በቀለ እና ርዮት
በሰላሙ መንገድ ህዝብን የሰበኩት
ነጻነትን ሲሹ ፍትህ የተጠሙት
ላገሩ በጮኸ ለፍትህ በጻፈ፣
እስክንድር ታሰረ ብዕሩ ነጠፈ።

ሀገር እየሸጡ ሀብት እየዘረፉ፣
በጅምላ እያረዱ ዘርን እያጠፉ፣
የጌቶቹ ልጆች ጮማ እየቆረጡ፣
ስንቶች ማደሪያ አጥተው ከቤታቸው
ወጡ።

እምዬ ንገሪኝ ምንድን ነው መርገምሽ፣
አልወጣልሽ ያለው መከራ ከቤትሽ።
ኀዘን ኀዘን ወልዶ ልቤን እየነካው፣
የትናንቱ ቁስል ሳይጠፋ ጠባሳው፣
ወደብ አልባ መሆን እያንገበገበኝ፣
ዛሬ ይባስ ብሎ ድጋሚ አስደፈረኝ።

ከእንግዲህ ይበቃል ምን ሊመጣ ሌላ፣
ዘር ቀለምን ሳልለይ ወይም እምነት ጎራ
አብሬ ልሰለፍ ከነአንዱዓለም ጋራ፣
እንደሰው ልቆጠር እኔም ታሪክ ልስራ።

**(በዳዊት መላኩ *ከጀርመን*)**